


# ገንዘብ ለመቆጠብ የተሻለ 9 ጠቃሚ ምክሮች

**የህዝብ ግንኙነት ዲቪዥን**

**ሚያዚያ/2016 ዓ.ም**

**ፊንፊኔ፣ኢትዮጵያ**

# ገንዘብ ለመቆጠብ የተሻለ 9 ጠቃሚ ምክሮች

ገንዘብ ቁጠባን ልምድ ማድረግ በህይወት ዉስጥ ለዉጥ ለማየት ወሳኝ መንገድ ነዉ። የምናገኘዉን ገቢ ይብዛም ይነስም እንዳለ ከማጥፋት የተወሰነዉን መቆጠብ ብዙ ጠቀሜታዎች አሉት። ለምሳሌ –

- ✓ ያልታሰብ ችግር ቢያጋጥም (መታመም፣ ከስራ መዉጣት፣ ንግድ መክሰር....) የሰዉ ፊት ሳናይ እንጠቀምበታለን
- ✓ ልንሰራዉ የምናስበዉ ቢዝነስ ቢኖር መነሻ ካፒታል ይሆነናል
- ✓ ዋጋዉ ከፍ ያለ ልንገዛዉ የምናስበዉ ነገር ቢኖር ይጠራቀምልናል (ቤት፣ መኪና፣ ወዘተ)

ጠቀሜታዎቹ እነዚህ ከሆኑ የሚቀጥለዉ ጥያቄ የሚሆነዉ ምን ብናደርግ የተሻለ መቆጠብ እንችላለን የሚለዉ ነው።

## 1. በጀት ማዘጋጀት

የመጀመሪያው ርምጃ በጀት ማዘጋጀት ነዉ።።በጀት ማለት ባጭሩ ገንዘቤን እንዴት እጠቀማለሁ የሚል እቅድ ማለት ነው። ይሄን ያህል ለኪራይ፣ ይሄ ለልጆች ትምህርት ቤት፣ ወዘተ።።በጀት ካዘጋጀን በኋላ ደግሞ ያን ወለም ዘለም ሳይሉ መከተል ያስፈልጋል። በወር 200 ብር ለመዝናኛ ብለን ካስቀመጥን በኋላ በስጋ ቤት ጋር ባለፍን ቁጥር ቁርጥ የሚያምረን ከሆነ ለቤት ኪራይ ያስቀመጥነዉን ብር ጨርሰን ካከራያችን ወር ሙሉ ስንደባበቅ እንከርማለን!

## 2. ወጪና ገቢን በደንብ ማወቅ

ምን ያህል ገንዘባችንን ምን ላይ ነዉ የምናወጣዉ? ይሄን ማወቅ የሚጠቅመዉ ቁጠባን ለመጨመር ወጪን መቀነስ ቢያስፈልገን ከየት ላይ መቀነስ እንደምንችል ስለሚያመላክተን ነዉ። ይሄን ለማድረግ ደግሞ ወጪና ገቢያችንን መዝግቦ መያዝ ያስፈልጋል።

**3. የሚጠቅመን ላይ ማተኮር**

ገንዘባችንን የምናወጣበትን ነገሮች በደንብ አዉቀን ለህይወታችን ካለን ህልም አንጻር የቱ አስፈላጊ ነዉ፣ የቱ ደግሞ ቢቀር አይጎዳም ብለን መወሰን አለብን። የቤታችንን ጣራ መቀየር እየፈለግን ጥቂት የማይባለዉን ገቢያችንን አዲስ መጣ የተባለ ፋሽን የሆነ ቀሚስ ወይም ሱሪ ላይ የምናጠፋ ከሆነ ክረምት ሲመጣ ባሊ መደቀን ነዉ የሚሆነዉ ትርፉ!

**4. መጀመሪያ ወደቁጠባ!**

ገንዘብ ሴቭ ማድረግ ለሚፈልግ ሰዉ ጥሩዉ ዘዴ ከወጪ የቀረዉን ባንክ ማስገባት ሳይሆን መጀመሪያዉኑ ሴብ ማድረግ የምንፈልገዉን መጠን ወስነን ያንን ቀንሰን ካስቀመጥን በኋላ ወጪያችንን በተረፈዉ ልክ ማድረግ ነዉ። አለበለዚያ ገቢያችን በየአመቱ ቢጨምር እንኳን ወጪያችን ከገቢያችን እኩል ያድግና ምንም ሳንቆጥብ እንቀራለን።

**5. እንደራሳችሁ እንጂ እንደጎረቤታችሁ አትኑሩ።**

ጎረቤቶቻችን ፍላት ስክሪን ቴሌቪዥን ሲገዙ እኛም ካማረን፣ ጓደኞችን ሂዉማን ሄር ስታረግ እኛም ካማረን – ህይወታችንን መቀየር የምንችልባቸዉን አጋጣሚዎች እናጣቸዋለን። የተሻለ ነገር መፈልጉ ችግር የለዉም ግን የቱ መቅደም አለበት የሚለዉ ላይ መጠንቀቅ ይገባል።

**6. አወዳድራችሁ ግዙ!**

እቃ ስትገዙ ሁሌ አንድ የለመዳችሁት በታ ከመሄድ ሌሎች አማራጮችን አይታችሁ የተሻለ ዋጋ ያለበትን መርጦ መገብየት

**7. እቃ ለመግዛት ስትሄዱ ሊስት ይዛችሁ ሂዱ (ከዚያ ፈቀቅ ማለት የለም!)**

ይሄንን ዲስፕሊን ካላዳበርን ሱቅ በሄድን ቁጥር የሚያብለጨልጭ ነገር አይጠፋምና ከእቅድ ዉጪ ላልተፈለገ ወጪ እንዳረጋለን። ልጆቻችሁንም ያማረ ሁሉ እንደማይገዛ አስተምሯቸው። ከገባቸዉ – ጥሩ! ካልሆነ ግን ሱቅ አትውሰዷቸዉ (አለበለዚያ ለምነዉም ሆነ አልቅሰዉ ያልታሰበበትን አሻንጉሊት መኪና ያስገዟችኋል!)

## 8. ዉድ እቃ ከመግዛታችሁ በፊት ጊዜ ወስዳችሁ አስቡበት።

k.com

ምናልባትም ሶፋ ልንገዛ ያሰብነዉ ቤታችን ያለዉ አርጅቶ ሳይሆን የጓደኛችን ልጅ ልደት ላይ የሚያምር አዲስ ፎቴ መግዛታቸዉን አይተን “ወይኔ! እኔስ!” ብለን ይሆናል። የተሰማን የመበለጥ ስሜት እያደር መክሰሙ አይቀርምና ልንቀይር ያሰብነዉ ሶፋ ያን ያህል አስፈላጊ አለመሆኑን አውቀን ልንጀምር ለምናስበዉ ቢዝነስ ወይም ልንገዛዉ የምንፈልገዉ መኪና ማጠራቀማችንን እንቀጥላለን።

## 9. ተጨማሪ ሃሳቦች

በነስ ወይም ሌላ ከወርሃዊ ደሞዛችሁ ተጨማሪ ገንዘብ ስታገኙ ለመቆጠብ ጥሩ አጋጣሚ ነው። ብዙ ሰዉ ግን ያገኘዉን በነስ “ብትንትን ብትንትን እንደጠላት ገንዘብ” ለማድረግ ጊዜ አይፈጅበትም። ሬስቶራንት ከመብላት ምሳችሁን ከቤት ይዛችሁ መሄድ – ቀላል የማይባል ገንዘብ ሊያድንላችሁ ይችላል። ሰዉም መጋበዝ ቢኖርባችሁ ቤት አዘጋጅቶ መጥራት “እንገሌ ክትፎ ቤት” ከምታወጡት ገንዘብ ጋር ሲነጻጸር የማንችስተር ሲቲ ና የሃደርስፊልድ ያህል ልዩነት አለዉ። ጥሩ እቃ እንጂ ታዋቂ ስም አታሳዱ። እርግጥ ታዋቂ ስምና ጥሩ እቃ አብረዉ የሚገኙባቸዉ አጋጣሚዎች በርካታ ናቸዉ። ይሁንና ክላርክ ወይም ካልቪን ክሌይን ካልሆን አይዋጥልንም ካልን እንቸገራለን። ይሄ ግን አቅሙ ያላቸዉን ሰዎች አይመለከትም።

በመጨረሻም – ገንዘብ መቆጠብ ባንክ ዉስጥ ይሄን ያህል አለኝ ብሎ ለማዉራት ሳይሆን ለቤተሰባችን የሚበጅ ጥሩ ቁምነገር ለመስራት ነው። ምን ያህል እንደምንቆጥብ፣ ለምን ያህል ጊዜ፣ ብሎም ምን እንደምናደርግበት ጥሩ እቅድ ያስፈልገናል። አለበለዚያ ብሩ ቁጭ ብሎ ቀን ባለፈ ቁጥር የመግዛት አቅሙ እየደከመ ይሄድና አተርፍ ባይ አጉዳይ እንሆናለን! ማድረግ ለምናስበዉ ነገር መቆጠብ ብቻ ግን በራሱ በቂ ላይሆን ይችላል። ገቢያችንን የምንጨምርበትንም መንገድ ጎን ለጎን መፈለግ ይገባል።

አስተያየታችሁን አካፍሉን። ሌሎች ዘዴዎች ካሏችሁ ኮሜንት ላይ ጻፏቸዉ። ምናልባትም ይህ መልእክት ለሌሎችም ሊጠቅም ይችላልና ሼር እንድታደርጉ ትብብራችሁን እንጠይቃለን።

Source

[www.bettermoneyhabits.com](www.bettermoneyhabits.com)